ኦሕኒኢአ

OPMEU

*የካቲት 23 ቀን 2011 ዓም*

## *ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት የቀረበ።*

## *ድሃ ተበደለ፣ፍትህ ጎደለ!!*

ወደ ዋናው ርዕሳችን ከመግባታችን በፊት ለአምዳችን ተከታታዮች እንኳን ለ123ኛ የአድዋ ድል በዓል አደረሳችሁ እያልን የአባቶቻችን የአንድነትና የፍቅር ዉጤት በደስታ ስናነሳ የዛሬ መሪዎቻችን አገር መከፋፈልና ሕዝባችንን ማጋደል በሐዘኔታ ማንሳታችን ሣንጠቁም አናልፍም፣ አባቶቻችን የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተባበር ጠላትን አፈር ሲያስግጡ የዛሬ መሪዎቻችን ግን በሕዝባችን መካከል የጥላቻ ግንብ ሊያስመርቁ እይኳተኑ ቢሆኑም ትላንት ታሪክ የሠራ ጀግናው የኢትዮጵያ እንደማይመለከት እናምናለን፡፡

አባቶቻችን የአስተዳዳሪን በደል ሲገልጹ ድሃ ተበደለ ይላሉ፣የብሶታቸው መግለጫ ነው፣ ተረቱ ከአከባቢው ዘልቆ ለአስተዳዳሪዎች በዳይ ይጠየቅና ተበዳይም ይቅርታ ይጠየቃል ወይም ይካሳል፡፡ ይህን መግለጫ እንድንጽፍ ያስጋደደን ዶር አቢይ በኢሕ አዴግ ወያኔ ተሰይሞ በሥልጣን ላይ ከወጣ ከቃላት ተስፋ ዘልቆ ለሕዝባችን በአገር ውስጥ ለሚገኙ የተደረገላቸው እንዳለ መስካሪው ሕዝባችን ነው፡፡የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት እንደ አንድ የኦሮሞ የፖለቲካ ፓርቲ የሚታገል ቢሆንም የኦሮሞ ሕዝብ ለብቻው ይበልጽግ የሚል አቋም የለውም፡ አቋሙ ወይም መሠረታዊ ዓላማው ታሪክን በተመረኮዘ ሆኖ ለአንድ ኢትዮጵያዊ ብሔር የሚደረግ እንዲደረግለት ነው፡፡

ድርጅታችን ኦሕንኢአ ከመጀመሪያው ኢትዮጵያውያን በጠሬጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ስለኢትዮጵያ መጻኢ እድል እንዲወያዩ ብዙ ጥቆማዎችን መስጠታችን ይታወሳል፡፡ይህን ስንል ደግሞ ሕዝባችንን የጨፈጨፈ አይጠየቅ፣ አገርን የዘረፈ ገንዘቡን አይመልስ፣ የተበደለ አይካስ ወዘተ ለማለት አይደለም፡፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተፈጸሙ ክስተቶች ለአንዱ ወገን ያላዳላ ውሳኔ ተሰጥቶበት ወደሚቀጥለው ምዕራፍ መሸጋገር ሲቻል ያለወቅቱና አላአስፈላጊ አጀንዳዎች መዘርጋት ከዚያም ግልቶ በመታየት ለዛሬ ግርግር እያበቃን ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱ ቀውሶችና አደገኛ ክንውኖች ተጠያቂው የኢትዮጵያ መንግሥት ነው፡፡ ወያኔ ለዘረፋ የዘረጋውን መረብ ሕዝባችን በጣጥሶ ቢጥልም የከፋ የዶር አቢይ ሲተካ ለውጡን በሰመረ መልኩ ማካሄድ ሲጋባው.......የኢሕ አዲግ ሕገ መንግሥት፥ አይቀየርም፣ ሕገመንግሥቱ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፣ ወዘተ ብሎ አወጀ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቡና ጥላቻው ከወያኔ ሕገመንግሥትና ፖሊሲ ጋር እንጂ ሰዎቹ ትግሬዎች ስለሆኑ ከትግሬዎች  ጋር ጠብ የለውም፡፡

በአሁኑ ወቅት መቀለ ሆነው የሚያፋጁን እነርሱ አዲስ አባባ ቢኖሩና ሕገመንግሥታቸውና ፖሊሲያቸው መቀለ ተወስዶ ቢቀበር የሚቃወም ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡

ዶር አቢይ ጠቅላይ ሚኒስተር ተብሎ በኢሕአዲግ ሲሰየም ያልተደሰተ ኢትዮጵያዊ የለም ...አቢይ አትበሉ ነቢይ በሉ....ብሎ ያልተናገረ የለም፡፡ ተስፋ የሚሰጥ ድስኩሩ ለአንድነትና ለአገር ብልጽግና ያለመ ይመስል ነበር፡፡ ዶር አቢይ ጠቅላይ ሚኒስተር ከጀመረ በኋላ የደረሱ ቀውሶች በጣም ብዙ ናቸው፣ መፈናቀሉ አለመጠን በዛ፥እርስበርስ መጋደሉ ተጠናክሮ ቀጠለ፣ ለሚፈጸሙ ችግሮች እጠያቂ ጠፋ፡፡ አብያተ ክርስቲያኖች ሲቃጠሉ፣ መስግዶች ሲፈርሱ ሲፈርሱ ....ሃይ ተው....አልተገኘም፡፡ ከሁሉ የሚያሳዝነው የለገጣፎ በቶች መፍረስ ነው፡፡ ከአሥር ዓመት በላይ ግብር የከፈሉ ሰዎች የቤታቸው ሲፈርስ ዶር አቢይም ሆነ ለማ መገርሳ..... አላወቅም አልሰማንም.....ማለታቸው ከኃላፊነት ለመሸሽ ያደረጉት ሤራ እንጂ ከአዲስ አባባ ከ15 ኪ ሜ የማይበልጥ የለገጣፎ ግፍ ሣያዩ ቀርተው አይደለም፡፡

ዶር አቢይ ስለለገጣፎ ሲናገር.....እኔ ስለ ለገጣፎ ጉዳይ አይመለከተኝም፣ እኔ የከተማ አስተዳዳሪ አይደለሁም ብሏል፡፡ እዚህ ያሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት (ኦሕንኢአ) ለዶር አቢይ የሚያቀርበው ጥያቄ፡

እኔ የከተማ አስተዳዳሪ ሲል በዚሁ ወር መግቢያ ላይ አራት ኪሎ በተመንግሥት ኦሮሞዎችን ብቻ በመሰብሰብ.....ፊንፊኔ የትግላችን መነሻ ስለሆነች የኦርሞ ሕዝብ ጥቅም ማስከበሪያ እናደርጋታለን... ብሎ እንደተናገረ ቭዲዮው ይመሰክራል፡አምቦ የሃገረ ሕይወት ዋና ከተማ ናት፡ዶር አቢይ የእጅ ሰዓቱን አዉልቆ ጨርታ አቅርቦ አሽጦ ብዙ ገንዘብ ማስገኘቱን እኛም ሐሳቡን እንደግፋለን በርታ በዚሁ ግፋበት እያልን........አምቦ ግን ከተማ መሆኗን ማንም ሊዘነጋው አይገባም.........

ድርጅታችን ኦሕንኢአ በልማት ስም ስለሚፈናቀሉት አጽንኦት ሰጥቶ የሚከራከረው ያለምክንያት አይደለም፣ ልማት አስፈላጊ ነው ፣ለአገር ይጠቅማል፣ ሕዝብን ያሳድጋል፥ ሕዝብን አፈናቅሎ፣ዜጎችን አስለቅሶና በአገራቸው ላይ እንዲዋረዱ አድርጎ የሚመጣ ልማት በአገራችን ብቻ እንጂ በሌሎች አገሮች አይታይም...........ቀጣዩ ስለ ፖ ለ ቲ ካ አ ት ና ገ ሩ የሚለው የመሪዎቻችን ተመሳሳይ ማስፈራሪያ እናቀርባለን................

ድ ል ለ ኢ ት ዮ ጵ ያ !!